የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ሐምሌ 26 2014

ቁጥር/REF NO: 01/2.56/306/14

ለሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና ማስፈፀሚያ መመሪያን ይመለከታል፤

ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀፅ 86 (5) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሃገራዊ ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን፣የሙያ ስነምግባር ደንቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሰራር ስነ ስርዓትን እንደሚያወጣ ይደነግጋል፡፡

በዚሁ መሠረት ለከፍተኛ ትምህርት አገራዊ ቅድመ-ምረቃ የመውጫ ፈተናን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋት እንዲቻል ይህንን የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና ማስፈፀሚያ መመሪያ ተዘጋጅቶና በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ መመሪያ ቁጥር 919/2014 ሆኖ የፀደቀ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
- ለከፍተኛ ትምህርት ብቃትና ጥራት ማሻሻያ ዴስክ

ትምህርት ሚኒስቴር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

# የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አፈጻጸም መመሪያ

## ቁጥር 919/2014

ሐምሌ 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አፈጻጸም መመሪያ

# ቁጥር 919/2014

## መቅድም

የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን የሚጠበቅባቸውን ብቃት ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአገራዊና በዓለማቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ምሩቃንን በሁሉም የትምህርት መስኮች ለማፍራት እንዲቻል፤

ከአካባቢያዊ፤ አገራዊና ዓለማቀፋዊ ኢኮኖሚ፤ ቴክኖሎጂ ዕድገትና ከማኅበረሰቡ ፍላጎት ጋር እያደገ የሚሄድ የትምህርት ስርዓተ በዘላቂነት ለመዘርጋት፤

እጩ ምሩቃን በእውቀት፤ በክህሎትና በአመለካከት በየምሩቃን ፕሮፋይል የተቀመጠውን ብቃት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ስለሚገባ፤

በፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላትን በአግባቡ ማሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ፣
## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 919/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የቃላት ፍቺ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

2.2 **"አገልግሎት"** ማለት የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ማለት ነው፡፡

2.3 **"ብቃት"** ማለት የአንድን ምሩቅ እውቀት፤ ክህሎት እና አመለካከት እንዲሁም ተገቢውን የመፈፀምና የማስፈጸም አቅም ወይም ችሎታ እና ተወዳዳሪነትን ያጠቃልላል፡፡

2.4 **"ፈተና"** ማለት የአንድን ተማሪ ብቃት ለመመዘን የምንጠቀምበት ትምህርታዊ ግምገማ ነው፡፡

2.5 **"የመውጫ ፈተና"** ማለት በማንኛውም የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂ ተማሪዎችን ብቃት ለመመዘን የሚሰጥ የማጠቃለያ ፈተና ነው።

2.6 **"የድጋሚ ፈተና"** ማለት በቅድሚያ የተሰጠውን የመውጫ ፈተና ወስደው የማለፊያ ነጥብ ላላገኙ ተፈታኞች በድጋሚ የሚሰጥ ፈተና ነው፡፡

2.7 **"እጩ ምሩቃን"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም የተማሩና የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን አጠናቀው የመውጫ ፈተና ለመውሰድ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎች ነው፡፡

2.8 **"የከፍተኛ ትምህርት ተቋም"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ትምህርት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

2.9 **"የፈተና ማዕከል አስተባባሪ"** ማለት በትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት የሚወከል ሆኖ በፈተና ማዕከላት ውስጥ ስራውን በበላይነት የሚመራና የሚስተባብር ነው፡፡

2.10 "የትምህርት መስክ ምድብ" ማለት የተፈጥሮ ሳይንስ ወይም ማህበራዊ ሳይንስ ምድብ ማለት ነው፡፡

2.11 የጾታ አገላለጽ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጹት ሁኔታዎች በሙሉ ለሴት ጾታም ያገለግላሉ፡፡

## 3. የመመሪያው አስፈላጊነት

የመጀመሪያ ዲግሪ የእጩ ምሩቃን የመውጫ ፈተናን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር፤ በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ ለመስጠት እና የተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 4. የመውጫ ፈተና ዓላማ

እጩ ምሩቃን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቆይታቸው በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተቀመጠውን የምሩቃን ፕሮፋይል ከዕውቀት፣ ከክህሎትና ከአመለካከት አንፃር በብቃት መጨበጣቸውን ለመመዘን ነው፡፡

### 4.1 ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፤

ሀ. ለትምህርት ጥራት ትኩረት በመስጠት የትምህርት ውጤታማነትን ማሻሻል፤

ለ. በከፍተኛ ትምህርት ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት፤

ሐ. በሁሉም የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ እጩ ምሩቃን ተገቢውን የብቃት ደረጃ ያሟሉ መሆናቸውን መመዘን፤

መ. በከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራሞች እና ተቋማት መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ መፍጠር ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት
# ለመውጫ ፈተና ብቁ ስለመሆን እና የፈተናው ሂደት

## 5. ለመውጫ ፈተው ብቁ ስለመሆን

5.1 እውቅናና ፈቃድ በተሰጣቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እውቅና ባላቸው የትምህርት ፕሮግራሞች የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ትምህርታቸውን ተከታትለው ያጠናቀቁ፤

5.2 ይህ መመሪያ ጸድቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት አሰጣጥ (Delivery Modalities) ትምህርታቸውን በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ተከታትለው ያጠናቀቁ፤

5.3 በከፍተኛ ትምህርት ቆይታቸው ሁሉንም ኮርሶች ወስደው ያጠናቀቁ ወይም የመጨረሻ ዓመት የሁለተኛ ሴሚስተር ላይ ተመዝግበው በመማር ላይ ያሉ፤

5.4 በመጀመሪያ ወይም በባለፈው ዙር ፈተና የማለፊያ ነጥብ ያላስመዘገቡና ድጋሚ እንዲፈተኑ የተመዘገቡ፤

## 6. ምዝገባና የፈተና አሰጣጥ ስርዓት

6.1 ከላይ በአንቀጽ 5 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተፈታኞች ለፈተናው በተቋማቸው በኩል ወይም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የበይነ-መረብ በኩል በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይመዘገባሉ፤

6.2 ተፈታኞች ከተመዘገቡ በኋላ በሚወጣው የመውጫ ፈተና ፕሮግራም መሰረት ለፈተናው በተዘጋጁት የፈተና ማዕከላት በአካል በመገኘት ይፈተናሉ፤

6.3 ፈተናውን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወስዱ የመደበኛ ተማሪዎች በተመረጡ የፈተና ጣቢያዎች ይፈተናሉ፤

6.4 የድጋሚ ተፈታኞች ፈተናውን ለመውሰድ ከመረጡት የፈተና ጣቢያ ውጭ በሌላ የፈተና ጣቢያ መፈተን አይችሉም፤

6.5 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈተናው በክላስተር ደረጃ ሊሰጥ ይችላል፡

6.6 ማንኛውም ተፈታኝ ለፈተና ሲቀርብ ማንነቱን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ካርድና ለፈተና የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጫ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 7. የመውጫ ፈተና አስተዳደር

7.1 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ ነጻነትን ሙሉ በሙሉ እስከሚያገኙ እና ፈተናውን በራሳቸው አቅም ማስተዳደር እስከሚችሉ ድረስ የመውጫ ፈተናው በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ይሰጣል፤

7.2 የሙያ ማህበራት ተጠናክረው ሙያዊ አበርክቶ መስጠት የሚችሉበት ደረጃ ሲደርሱ በመውጫ ፈተናው ውጤታማነት ላይ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ስልት ይዘጋጃል፤

7.3 በተለያየ ምክንያት የመውጫ ፈተና ያልተፈተኑትን ጨምሮ ፈተናው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰጣል፤ ሆኖም ግን እንደ ትምህርት ፕሮግራሞች ልዩነት የመውጫ ፈተናው በዓመት ከዚህም በላይ ሊሰጥ ይችላል፤

7.4 በሙያ ማህበራት ወይም በሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ የሙያ ፈቃድ ማረጋገጫ ፈተናዎች ጋር የመውጫ ፈተናውን በቅንጅት ሊሰጥ የሚችልበት ስልት ሊቀየስ ይችላል፡፡

## 8. በመውጫ ፈተናው የሚሸፈኑ የብቃት ወሰኖች

8.1 የምሩቃን የመውጫ ፈተና ሲዘጋጅ እንደየ ትምህርት መስኩ ባህሪ በስነ ትምህርት በሚታወቁት የብቃት ወሰኖችን (Scope of Learning Domains) መሰረት ይዘጋጃል፤

8.2 የመውጫ ፈተናው አዘገጃጀት በዋናነት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተገለጹትን ቁልፍ የመማር ውጤቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤

8.3 የፈተናው ይዘት በትምህርት መስኩ ባለሙያዎች እና በሳይኮሜትሪ ወይም በስነ-ልኬትና ግምገማ (Measurement and Evaluation) ባለሙያዎች ይገመገማል፤

## 9. የመውጫ ፈተናው ይዘትና የሚያካትታቸው ኮርሶች

9.1 ፈተናው የምሩቃንን ፕሮፋይል፣ እንደ ትምህርት መስኩ ባህሪ በስነ ትምህርት በሚታወቁት የብቃት ወሰኖች (Scope of Learning Domains) መሰረት ያደረገ ሆኖ ይዘጋጃል፤

9.2 በመውጫ ፈተናው ውስጥ የሚካተቱት የትምህርት ዓይነቶች በየትምህርት መስኩ በሚዘጋጁ የማስፈጸሚያ ማንዋሎች ላይ እንዲገለጹ ይደረጋል፡፡

9.3 በፈተናው የሚካተቱት ኮርሶች ምሩቃን በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት እንዲጨብጧቸው የሚፈለገውን የምሩቃን ፕሮፋይልን የሚለኩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 10. ፈተናው ስለሚሰጥበት አግባብ

10.1 ፈተናው የጹሑፍና የተግባር ላይ ፈተናን ሊያካትት ይችላል፤ ለፈተናው የሚኖራቸው የነጥብ ድርሻ በየፕሮግራሙ በሚዘጋጀው የፈተና መከታተያ ንድፈ-መለኪያ ላይ (Blue Print) ይገለጻል፤

10.2 ልዩ ብቃትና ዕውቀት ለመመዘን በሚጠይቁ ፕሮግራሞችና የትምህርት መስኮችን የሚለኩ የፈተና ተቋማት ይለያሉ፤

10.3 እንደ ትምህርት መስኩ የተለያየ ሆኖ የተግባር ላይ ፈተና ይዘት በሁሉም ፕሮግራሞች ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ የጹሑፍ ፈተና በስራ ላይ ይውላል፤

10.4 የጹሑፍ ፈተናው የምርጫ ጥያቄዎችን (Multiple Choice items) እንዲያካትት ሆኖ ይዘጋጃል፤

10.5 ከላይ በአንቀጽ 10.4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ትምህርት ፕሮግራሙ ዓይነት የፈተናው ይዘትና ቅርጽ ሊለያዩ ይችላሉ፤

10.6 በምርጫ መልክ የሚዘጋጁት ጥያቄዎች የተፈታኞችን እውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት በትክክል የሚለኩ መሆናቸውን በዘርፉ ባለሙያዎች ይገመገማሉ፤

10.7 ፈተናው በቴክኖሎጂ፤ በበይነ መረብ፤ በወረቀት ወይም ቅይጥ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊሰጥ ይችላል፤

## 11. ድጋሚ ስለመፈተን

11.1 ተፈታኞች ፈተናውን ወስደው ማለፍ እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ላልተገደበ ጊዜ መፈተን ይችላሉ፤

11.2 ተፈታኞች ፈተናውን በድጋሚ ለመውስድ ዝግጁ በሆኑበት ጊዜ አመልክተው መፈተን ይችላሉ፡፡

## 12. የፈተናው ፋይዳ/ተጽዕኖ

12.1 በሁሉም የትምህርት መስኮች የማለፊያ ነጥብ ሳይንሳዊ መንገድን የሚከተል ሆኖ 50% ዝቅተኛው የማለፊያ ነጥብ ይሆናል፤

12.2 እንደ ትምህርት መስኩ ተጨባጭ ሁኔታ ከ50% በላይ የማለፊያ ነጥብ ለሚጠይቁ መስኮች የማለፊያ (የመቁረጫ) ነጥቡ በየጊዜው ሊወሰን ይችላል፤

12.3 የመውጫ ፈተና ውጤት በተማሪዎች ሰርተፊኬት (Temporary Degree) ወይም ትራንስክሪፕት ላይ አልፏል (Pass) ወይም ወድቋል (Fail) በሚል እንዲመላከት ይደረጋል፤

12.4 አንድ ተማሪ ለምረቃ ብቁ የሚሆነው የመውጫ ፈተና ወስዶ የማለፊያ ነጥብ ካሟላ ብቻ ይሆናል፡፡

12.5 በአንቀጽ 11.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመውጫ ፈተና ወስደው የማለፊያ ነጥብ ያላገኙ ተፈታኞች በብሔራዊ የብቃት ማዕቀፍ በሚሰጠው እኩሌታ መሰረት ተገቢው ማስረጃ ይሰጣቸዋል፤

## 13 ፈተና ለማዘጋጀት የሚጠበቅ መስፈርት

በሁሉም የትምህርት መስኮች የመውጫ ፈተናውን የሚያዘጋጁ አካላት የሚከተለው ፕሮፋይል ሊኖራቸው ይገባል፡፡

13.1 በዩኒቨርሲቲ መምህርነት ቢያንስ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ያለው፤

13.2 በትምህርት መስኩ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው፤

13.3 በትምህርት መስኩ እና በምዘናና ግምገማ ትምህርት ዘርፍ በቂ እውቀት ያለው፤

13.4 የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (HDP) የተከታተለ፤

13.5 ከተቋሙ የስነ ምግባር ጉድለት የሌለበት፤

## 14 የድጋሚ እርማት

14.1 በፈተናው የመጀመሪያ እርማት ላይ ቅሬታ ያላቸው ተፈታኞች በተቋማት በኩል ወይም በበይነ-መረብ ቅሬታቸውን ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ማቅረብ ይችላሉ፤

14.2 ከቅሬታዎች መካከል የድጋሚ እርማት ጥያቄ ከቀረበ ፈተናው በድጋሚ ታርሞ ውጤቱ ለተፈታኞች ይገለጻል፤

14.3 በበይነ መረብ ለሚሰጡ ፈተናዎች የድጋሚ እርማት ጥያቄዎች አይስተናገዱም፤

## 15. አዎንታዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተፈታኞች

15.1 አዎንታዊ ድጋፍ የሚደረግላቸው ተማሪዎች ቀድመው ይለያሉ፤

15.2 አዎንታዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መረጃቸው በምዝገባ ወቅት ለአገልግሎቱ የሚደርሱበት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፤

15.3 ሁሉም ተቋማት ለተማሪዎቻቸው የሚያስፈልገውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤ አገልግሎቱ ደግሞ ድጋፉ መሟላቱን ያረጋግጣል፤

15.4 የሚደረጉ አዎንታዊ ድጋፎች ዝርዝር ሁኔታ በሚዘጋጀው የፈተና ማንዋል (Exam Handbook) ውስጥ በአግባቡ ይገለጻሉ፡፡

# ክፍል ሦስት

## የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 16 የትምህርት ሚኒስቴር

16.1 የእጩ ምሩቃን የመውጫ ፈተናውን አስተዳደር በኃላፊነት ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡

16.2 የሚመለከታቸውን አካላት በማማከር የመውጫ ፈተናውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀርጻል፤ አገራዊ መመሪያዎችንም ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡

16.3 የመውጫ ፈተና ስራውን ለማከናወን የሚረዳ በጀት በተቋማት በኩል እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

16.4 ከፈተና ዝግጅት እስከ ህትመት ድረስ የሚኖረው ሂደት ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ እንዲከናወን ስልቶችን ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

16.5 ፈተናው የሚሰጥባቸውን ተቋማት ዝርዝር ያሳውቃል፤ በፈተናው ወቅት የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችን እና ተፈታኞችን ይወስናል፤

16.6 ለፈተና አስፈላጊ ቁሳቁሶች በተቋማት (በፈተና ማዕከላት) መሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

16.7 ከተቋማትና ከአገልግሎት ሰጪው አካል ጋር በመመካከር የመውጫ ፈተና የሚሰጥባቸውን ቀናት ይወስናል፤ የፈተና መርሐ ግብር በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

16.8 ከአገልግሎቱና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመሆን ፈተናው በበይነ-መረብ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

16.9 በየፈተና ማዕከላቱ ፈተናው ያለምንም ችግር እንዲከናወን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

16.10 ፈተናውንና የፈተና ውጤቱን ይተነትናል፤ የትንተና ውጤቱን መሰረት በማድረግ ለተለያዩ ጥናታዊ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል፤ ለፖሊሲና ስትራቴጂ ስራዎች በግብዓትነት ይጠቀማል፤

16.11 ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ጋር በመሆን የፈተና ማንዋል (Exit Exam Handbook) ያዘጋጃል፤ ለሁሉም የባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

16.12 የመውጫ ፈተና መረጃዎችን ያደራጃል፤ በአግባቡ ይይዛል፤ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፤

16.13 የተፈታኞችን ምዝገባና ፈተና እንዲሁም ውጤትን በበይነ-መረብ ለማካሄድና ለማሳየት የሚያስችል ሶፍት ዌር (Software) ያዘጋጃል፤ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

16.14 በመውጫ ፈተና ዙሪያ ውጤታማ ስራዎችን ላከናወኑ ተቋማትና ግለሰቦች ዕውቅና የሚሰጥበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

16.15 በየዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ያቀርባል፤ ያስገመግማል፤ የቀጣይ አቅጣጫዎችም ይቀመጣል፡፡

## 17 የፈተና አሰጣጥ ቴክኒካል ኮሚቴ

17.1 ቴክኒካል ኮሚቴው አስራ አንድ አባላት ሲኖሩት አወቃቀሩም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. የከፍተኛ ትምህርት የብቃትና ጥራት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ .... ሰብሳቢ

ለ. ከኢትዮጵያ ትምህርት ምርምር ኔትወርክ (አንድ ተወካይ) ...... አባል

ሐ. ከኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርትና የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ማህበር (ሁለት ተወካይ)................................................... አባል

መ. ከትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን (አንድ ተወካይ) ............ አባል

ሠ. ከመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካዮች (አራት) .. አባል

ረ. የትምህርት ጥራት አማካሪ ምክር ቤት (አንድ) .................. አባል

ሰ. ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት (አንድ ተወካይ) .. ጸሐፊ

ቴክኒካል ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፡-

17.2 ከመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወከሉ አባላት የተቋማትን በተልዕኮና በትኩረት መስክ ልየታን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ይሆናል፤

17.3 እንዳስፈላጊነቱ ኮሚቴው ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደገና ሊዋቀር ይችላል፤

17.4 ፈተናው ከመሰጠቱ አስቀድሞ ፈተናው በሚሰጥባቸው ተቋማት ለፈተና ስራ የሚመጥን መሰረተ ልማት መሟላቱን ያረጋግጣል፤

17.5 በተገቢ ሁኔታ መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸውን ተቋማት/ የፈተና ማዕከላት በመለየት እንዲሟሉ ጥረት ያደርጋል፤ ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ሲያጋጠሙ ለሚኒስቴሩ በሪፖርት ያሳውቃል፤

17.6 ፈተናው በተቀመጠው ጥራት ስለመዘጋጀቱ እንዲሁም የፈተናውን ሂደት ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤

17.7 የአፈፃጸም ሪፖርትን በጽሁፍ ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

## 18 የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት

18.1 የመውጫ ፈተና በገለልተኛነት የሚሰራ መንግስታዊ ተቋም እስከሚቋቋም ድረስ አገልግሎቱ ፈተናውን በውክልና የማስተዳደር ኃላፊነት ይኖረዋል፤

18.2 በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ የተፈታኞችን ሙሉ መረጃ እና የፈተና ውጤቶችን ያደራጃል፤ በአግባቡ ይይዛል፤ ለተፈታኞችና ተቋማት በወቅቱ ያሳውቃል፤

18.3 በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የድርጊት መርሐ-ግብር ተግባራዊ ያደርጋል፤

18.4 የፈተና ማዕከላት አስተባባሪዎችን፤ ሱፐርቫይዘሮችንና ፈታኞችን ይመርጣል፤ በፈተና ማዕከላት ይመድባል/ያሰማራል፤

18.5 በፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲገጥም ከትምህርት ሚኒስቴርና ለዚሁ ተብሎ በተቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ ጋር በመቀናጀት ችግሮችን ይፈታል፤

18.6 ፈተናውን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ወጪ የሚያሳይ ፕሮፖዛል ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድለትም በፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት ስራ ላይ ያውላል፤

18.7 የፈተና ውጤትን ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል፤

18.8 በአገልግሎቱ ደረጃ ምላሽ ለሚያስፈልጋቸው ቅሬታዎች ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፤ ሪፖርትም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፤

18.9 የመውጫ ፈተናው በበይነ-መረብ የሚሰጥ ከሆነ የአገልግሎቱን ኃላፊነት የኢትዮጵያ የትምህርትና ምርምር ኔትወርክ ይረከባል፡፡

## 19 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

19.1 በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ትምህርታቸውን ተምረው ያጠናቀቁ እጩ ምሩቃንን ለፈተናው ይመዝግባሉ፤ ዝርዝሩንም ለአገልግሎቱ ወይም ለትምህርት ሚኒስቴር ያሳውቃሉ፤

19.2 የዩኒቨርሲቲውን ድህረ-ገፅ እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለተፈታኞች በወቅቱ ተደራሽ ያደርጋሉ፤

19.3 የድጋሚ ተፈታኞቻቸውን ይመዘግባሉ፤ የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ የመፈተኛ ክፍያን ሰብስበው ለአገልግሎቱ ገቢ ያደርጋሉ፤

19.4 የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመውጫ ፈተና የሚደረግ ወጪን ለመሸፈን ከተማሪዎች/ ተፈታኞች በአገሪቷ የፋይናንስ ህግ መሰረት ገንዘብ ሊሰበስቡ ይችላሉ፤

19.5 እጩ ምሩቃኖቻቸውን ለመውጫ ፈተናው ያዘጋጃሉ፤ የሞዴል ፈተናም ይሰጣሉ፤

19.6 የመውጫ ፈተናውን ያላለፉ ተማሪዎቻቸውን በድጋሚ ለፈተናው ያዘጋጃሉ፤

19.7 የአፈፃጸም ሪፖርትን በየጊዜው ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ያቀርባሉ፡፡

## 20 የፈተና ማዕከላት

20.1 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች መ/ቤቶች በፈተና ማዕከልነት ሊመረጡ ይችላሉ፤

20.2 የፈተና ማዕከላት ፈተናውን ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀትና መሰረተ-ልማት እንዲሁም ተፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው በቴክኒካል ኮሚቴ በኩል ተገምግሞ ሲረጋገጥ በማዕከልነት ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

20.3 ተቋማት ተፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው የሚረጋገጠው ተፈታኞች የመፈተኛ ማዕከላትን ከመምረጣቸው በፊት ይሆናል፡፡

20.4 ፈተናውን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት እንዲቻል የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡

20.5 ከፈተና ማዕከሉ አስተባባሪ ጋር በቅርበት ይሰራሉ፡፡

## 21 በፈተና አሰጣጥ ስራ ላይ የሚሳተፉ አካላት ሥልጣን እና ተግባር

### 21.1 የፈተና ማዕከል አስተባባሪ

ተጠሪነቱ ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ. የፈተና ማዕከሉን የፈተና ስራ በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ያስተባብራል፡፡ ችግሮችም ሲፈጠሩ መፍትሔ ይሰጣል፤ ከአቅም በላይ ሲሆን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

ለ. ፈተናውን በሚስጥራዊነት ለመስጠት እንዲቻል በአገልግሎቱ የሚሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ይወጣል፡፡

ሐ. የፈተና ጥያቄ ወረቀቶች፣ የመልስ ወረቀቶች እና ልዩ ልዩ ቅፆችን በአግባቡና በሚስጥራዊነት ይይዛል፤ ለሚፈጠረውም ችግር ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

መ. በአገልግሎቱ በመገኘት ስለ ፈተና አሰጣጥ ሂደት ገለጻ ይወስዳል፤ ለፈተና የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን /ሰነዶችን/ በኃላፊነት ይረከባል፡፡

ሠ. የመፈተኛ ክፍሎች እና አካባቢው ለፈተና አሰጣጥ አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ረ. ፈተናው በበይነ-መረብ የሚሰጥ ከሆነ ፈተናውን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

ሰ. የፈተናውን አሰጣጥ በተመለከተ ለሱፐርቫይዘር፤ ለፈታኝ፤ ለፀጥታ አስከባሪዎችና ለተፈታኞች ገለጻ ይሰጣል፡፡

ሸ. የፈተና መርሐ-ግብሩን ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ይፋ ያደርጋል፤ ፈታኝና ሱፐርቫይዘር በመመደብ በስራው ላይ እንዲሰማሩ ያደርጋል፡፡

ቀ. በፈተና ማዕከሉ ውስጥ ያሉ ተፈታኞችን፤ ፈታኞችን፤ ሱፐርቫይዘሮችን እና የፀጥታ አስከባሪዎችን ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

በ. በፈተና አሰጣጥ ወቅት በግልም ሆነ በቡድን የሚፈፀሙ ጥፋቶችን ከፈታኞችና ከሱፐርቫይዘሮች ጋር በመሆን አስፈላጊውን የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤ በቅጽ ሞልቶም ለአገልግሎቱ ያሳውቃል፡፡

ተ. በፈተናው ላይ ለተሳተፉና ክፍያቸው በአስተባባሪው በኩል የሚከፈላቸው ተሳታፊዎችን በመለየት የፋይናንስ ህግን ተከትሎ ክፍያውን ይፈጽማል፡፡

ቸ. ከፈተና ማዕከላት የመልስ ወረቀት የያዙ ፖስታዎች የታሸጉበትን ሸራዎች/ፖስታ በመተማመኛ ፈርሞ ለአገልግሎቱ ያስረክባል፡፡

ኀ. የፈተና አፈጻጸም ሪፖርት ለአገልገሎቱ ያቀርባል፡፡

## 21.2 ሱፐርቫይዘር

ተጠሪነቱ ለፈተና ማዕከሉ አስተባባሪ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ. ፈታኞችንና ተፈታኞችን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ ፈተናው በተያዘለት አግባብ መካሄዱን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙንም ለማዕከሉ አስተባባሪ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ለ. የመፈተኛ ክፍሎች ለፈተና አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ሐ. ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት ከፈታኝ መምህሩ ጋር በመሆን የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል፤ ከአቅም በላይ ሲሆን ለአስተባባሪው ያሳውቃል፡፡

መ. ፈታኝ በተጓደለበት ጊዜ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፈታኝነት ተመድቦ ሊሰራ ይችላል፡፡

ሠ. የፈተና ሥርዓትን ጉድለት የፈፀመ ፈታኝና ተፈታኝ ሲያጋጥም የፈተና ደንብ መተላለፊያ ቅጾችን በመሙላት ወዲያውኑ ለአስተባባሪው ያሳውቃል፡፡

ረ. በአገልግሎቱ በኩል የተሰጡትን የሱፐርቫይዘሮች ኃላፊነትና ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 21.3 ፈታኝ

ተጠሪነቱ ለሱፐርቫይዘሩ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ. የመፈተኛ ክፍሎች ለፈተና አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለ. የተፈታኞቹን የፈተና መግቢያ ካርድ እና መታወቂያ በማየትና በማረጋገጥ ያስገባል፡፡

ሐ.ተፈታኞችን በየመፈተኛ ቦታቸው ላይ ያስቀምጣል፤ የፈተና ሂደቱንም ይቆጣጠራል፡፡

መ. ማንኛውንም ዓይነት የፈተና ደንብ የተላለፈ ተፈታኝ ሲያጋጥም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ቅፅ ላይ በመሙላትና በመፈረም ለሱፐርቫይዘሩ ያቀርባል፡፡

ሠ. የፈተናውን መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ሰዓት ያስከብራል፤ በየመሐሉ ፈተናውን ለማጠናቀቅ የቀረውን ጊዜ ለተፈታኞች ያሳውቃል፡፡

ረ. በፈተናው ህግ የተከለከሉ ተግባራትን ማከናወን አይችልም፡፡

ሰ. በሱፐርቫይዘሩ የሚሰጠውን ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 21.4 የጸጥታ አካላት

ተጠሪነቱ ለፈተና ማዕከሉ አስተባባሪ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፤

ሀ. በፈተና ማዕከሉ በመገኘት ከመፈተኛ ክፍል ውጪ (በፈተናው ማዕከል ግቢ እና በዙሪያው) ያለውን ለፈተና አሰጣጡ ሂደት አዋኪ የሆነን ማናቸውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሲሆን ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

ለ. ከማዕከሉ አስተባባሪ ጋር በመሆን ተገቢውን የፈተና ሥነ-ሥርዓት የማስከበር ስራን ያከናውናል፡፡

ሐ. ከፈተናው ማዕከል አስተባባሪ በሚቀርብለት ጥያቄዎች መሰረት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

መ. ለእርዳታ ካልተፈለገ በስተቀር ወደ መፈተኛ ክፍሎች መግባት ወይም መጠጋት አይችልም፡፡

ሠ. የፈተና እና የመልስ መስጫ ወረቀቶች በአግባቡ ይጠብቃል፤ ችግር ሲፈጠርም ለአስተባባሪው ያሳውቃል፤

# ክፍል አራት

## ለፈተናው የሚያስፈልገው በጀት እና የክፍያ አፈፃፀም

### 22. ለምዘናው የሚያስፈልገው የበጀት ምንጭ

22.1 ለእጩ ምሩቃን ለሚሰጠው የመውጫ ፈተና በጀት እና የበጀት ምንጭ በሁለት ይከፈላል፤

ሀ. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህታቸውን አጠናቀው ለመጀመሪያ ጊዜ የመውጫ ፈተና ለሚወስዱ ተፈታኞች የፈተና ማስፈጸሚያ በጀት በተማሩበት ተቋም በኩል የሚሸፈን ይሆናል፤ ይህም በተማሪዎች የወጪ መጋራት ላይ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

ለ. ለድጋሚ ፈተና የሚቀመጡ ተፈታኞች የፈተናውን ሙሉ ወጪ በጊዜው የገበያ ዋጋ በመሸፈን ፈተናውን የሚወስዱ ይሆናል፡፡

ሐ. በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኩል ፈተናውን የሚወስዱ ተፈታኞች ለፈተናው የሚያስፈልገውን ወጪን በተፈታኞች ይሸፈናል፡፡

### 23. የበጀት አስተዳደር ስርዓት

23.1 የበጀት አስተዳደር ስርዓቱ የመንግስትን የፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት አድርጎ የሚፈጸም ሲሆን ፈተናውን ለማስተዳደር የሚውል ይሆናል፡፡

23.2 ፈተናውን ለማስተዳደር የሚውል የክፍያ ተመን በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ይወሰናል፡፡

23.3 ለፈተና ስራው የሚወጡ ወጪዎች በመንግስት የፋይናንስና ግዢዎች መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

23.4 የመውጫ ፈተናውን በዘላቂነት ተግባራዊ ለማድረግ እና ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል ህጋዊ የክፍያ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 24. ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማንኛውም ሁኔታ የጣሰ፤ እንዲጣስ ያደረገ፤ በማንኛውም ደረጃ ያለ አስፈጻሚና ፈጻሚ አካል በአገሪቱ ባሉ ህጎች፤ ደንቦችና አስተዳደራዊ መመሪያዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 25. የተፈፃሚነት ወሰን

25.1 ይህ የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና መመሪያ በሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ በተሰጣቸው የትምህርት መስኮች የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህታቸውን ተከታትለው ያጠናቀቁ ተማሪዎችን ይመለከታል፡፡ መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት መስጫ ዘዴዎች (Modalities) ትምህርታቸውን የተከታተሉ እጩ ምሩቃን ፈተናውን ይወስዳሉ፡፡

25.2 ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስትና ከሚመለከተው የመንግስት አካል ህጋዊ ፈቃድ የተሰጣቸው የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

25.3 ይህ የመውጫ ፈተና ከ 2015 ዓ.ም ጀምሮ የቅድመ ምረቃ እጩ ምሩቃን ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### 26. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያውን በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 27. መመሪያውን ስራ ላይ ስለማዋል

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 1/2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስትር